የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ–ሕዳር ፩ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 4
ADDIS ABABA - 10th Nov., 1998

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፺፩ ዓ.ም
የአዋሽ ተፋሰስ ውኃ ሀብት አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ገጽ ፰፻፶፮

CONTENTS

Proclamation No. 129/1998
Awash Basin Water Resources Administration Agency Establishment Proclamation ........ Page 856

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፺፩
### የአዋሽ ተፋሰስ ውሀ ሀብት አስተዳደር ድርጅት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአዋሽ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኘውን የየብስ ውሀ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም የሚያስተባብር ፣ የሚያስተዳድር ፣ የሚያከፋፍልና የሚቆጣጠር ድርጅት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአዋሽ ተፋሰስ ውሀ ሀብት አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፱/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ ፣

፩· "ቦርድ" ማለት የአዋሽ ተፋሰስ ውሀ ሀብት አስተዳደር ድርጅት ቦርድ ነው ፣
፪· "ሚኒስትር" እና "ሚኒስቴር" ማለት እንደቅደምተከተሉ የውሀ ሀብት ሚኒስትር እና ሚኒስቴር ነው ፣
፫· "ተፋሰስ" ማለት የአዋሽ ተፋሰስ ነው ፣
፬· "የውሀ ሥራዎች" ማለት የውሀ ሀብትን ለማጥናት ፣ አገልግሎት ላይ ለማዋል ፣ ለመቆጣጠር ወይም ለመጠበቅ የሚከናወኑ ሥራዎች ማለት ሲሆን ከዚሁ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሥራዎችን ይጨምራል ።

### PROCLAMATION 129/1998
### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE AWASH BASIN WATER RESOURCES ADMINISTRATION AGENCY

WHEREAS, it has become necessary to establish a government agency for the purposes of co-ordinating, administering, allocating and regulating the utilization of the surface water resources of the Awash Basin;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This proclamation may be cited as the "Awash Basin Water Resources Administration Agency Establishment Proclamation No. 129/1998."

2. *Definitions*

In this Proclamation:

1) "Board" means the Awash Basin Water Resources Administration Agency Board;
2) "Minister" and "Ministry" means the Minister and Ministry of Water Resources respectively;
3) "Basin" means the Awash River Basin;
4) "Water Works" means activities which undertake studies on water resources, regulate or control the use of water, and includes any other activities relating with it.

፫· *መቋቋም*

፩· የአዋሽ ተፋሰስ ውሀ ሀብት አስተዳደር ድርጅት/ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" ተብሎ የሚጠራ/እራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

፪· ድርጅቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል ።

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአሚባራ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላሉ ።

፭· ዓላማ

የድርጅቱ ዋና ዓላማ በተፋሰስ ውስጥ የሚገኘውን የየብስ ውሀ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም ማስተባበር ፤ ማስተዳደር ፤ ማከፋፈል እና መቆጣጠር ይሆናል ።

፮· የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር

ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙንና ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሀን ያስተዳድራል ፤ የወንዞቹን አፈሳሰስ ይቆጣጠራል ፤

፪· በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሱ ውሀዎች ላይ የውሀ ሥራዎች ለመሥራትና በጥቅም ላይ ለማዋል አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል ፤ ይቆጣጠራል ፤

፫· ፈቃድ ላላቸው ተጠቃሚዎች ውሀ ያከፋፍላል ፤ መንግሥት በሚወስነው ተመን መሠረት የውሀ ጅምላ ክፍያ ያስከፍላል ፤

፬· የዋና መስኖ አውታሮችና የዋና መስኖ መንገዶች ጥገና ሥራ ያከናውናል ፤ ለሚሰጠውም አገልግሎት በመንግሥት በሚወሰን መመሪያ መሠረት ተጠቃሚዎችን የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል ፤

፭· አግባብ ካላቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በመስኖ ውሀ አጠቃቀም አንጻር ጥናቶችን በማካሄድ የተሻሻሉ የውሀ ማኔጅመንት ዘዴዎችን ያመነጫል ፤

፮· በመስኖ ልማት ሥራዎችና ፕሮጀክቶች አካባቢ ጨዋማነት እንዳይከሰት የከርሰ ምድር ውሀ እንቅስቃሴን በመቆጣጠር እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

፯· የመስኖ ውሀ ማከፋፈያና ማስወገጃ ሀዳጐች ፤ የማግለያ ግድቦች ፤ የውሀ መቆጣጠሪያ በሮችና የጐርፍ መከላከያ ዱጋዎች የሚኒስትሩ መሥሪያ ቤት በሚያወጣው የደህንነት ደረጃ መሠረት መሠራታቸውን ያረጋግጣል ፤ ይቆጣጠራል ፤

፰· በተፋሰሱ ውስጥ ጐርፍ አደጋ የሚያደርስባቸውን ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ባለማቋረጥ በሚሰበሰቡ መረጃዎች አማካይነት በማጥናት የመከላከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል ፤ ለዘለቄታ ለመከላከል የሚያስችሉ ሥራዎችንም በእቅድና በተከታታይ ይሠራል ወይም እንዲሰሩ ያደርጋል ፤

፱· የንብረት ባለቤት ይሆናል ፤ ውል ይዋዋላል ፤ በስሙ ይከሳል ፤ ይከሰሳል ፤

፲· ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮችን ያከናውናል ።

፯· የድርጅቱ አቋም

ድርጅቱ ፤

፩· ቦርድ ፤

፪· በቦርዱ አቅራቢነት በሚኒስትሩ የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፥ እና

፫· አስፈላጊው ሠራተኞች

3. *Establishment*

1) The 'Awash Basin Water Resources Agency (hereinafter "the Agency") is hereby established as an autonomous public agency having its own legal personality.
2) The Agency shall be accountable to the Minister.

4. *Head Office*

The Agency shall have its Head Office in Amibara, and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. *Objectives*

The objectives of the Agency shall be to co-ordinate, administer, allocate and regulate the utilization of the surface water resources of the Basin.

6. *Powers and Duties of the Agency*

The Agency shall have the following powers and duties:

1) to administer the available water of the Basin that flows across or lies between more than one Regional Governments and regulate the flow of water of such rivers;
2) to issue permits pursuant to appropriate law, to construct and operate water works, in relation to waters referred to in sub-Article (1) of this Article and regulate same;
3) to allocate water to permittees and collect bulk charges for water use as determined by the Government;
4) to undertake the maintenance of primary irrigation networks and main service roads and collect fees in accordance with a directive issued by the government;
5) to initiate improved water management methods, in co-operation with the appropriate institutions, by conducting studies pertaining to uses of water for irrigation;
6) to cause measures to be taken by monitoring ground water level in order to prevent an occurrence of salinity problem in areas where irrigation development works and projects are carried out;
7) to ensure and regulate the construction of irrigation water distribution and drainage structures; diversion dams; water control gates and dyks in accordance with safety standards to be issued by the Ministry,
8) to cause preventive measures to be taken by conducting studies based on continuously collected data pertaining to flood situations and incidents that causes damage within the basin and carry out or cause to be carried out such planned and successive works having a permanent nature in order to prevent same.
9) to own property, to enter into contracts; to sue and be sued in its own name;
10) to carry out other activities as are necessary for the attainment of its objectives.

7. *Organization of the Agency*

The Agency shall have:

1) a board;
2) a General Manager to be appointed by the Minister

፰· <u>የቦርዱ አባላት</u>

፩· ቦርዱ ከዘጠኝ የማይበልጡ አባላት ይኖሩታል ።

፪· የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት አግባብ ካላቸው ተቋሞች በመንግሥት ይሰየማሉ ።

፱· <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ እና ፮ የተመለከቱት የድርጅቱ ዓላማዎች እንዲሁም ሥልጣንና ተግባሮች በሚገባ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፤ ያረጋግጣል ፤

፪· የድርጅቱን ድርጅታዊ መዋቅር እና ድርጅቱ የሚተዳደርበትን መመሪያ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል ፤

፫· በድርጅቱ ተቀርጸው የሚቀርቡ መመሪያዎችን ይገመግማል ፤ በሚኒስትሩ ሲጸድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል ፤

፬· ድርጅቱ የሚስፋፋበትን ፤ የሚጠናከርበትንና አሠራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ ይቀይሳል ፤

፭· በድርጅቱ እቅድና ረቂቅ በጀት እና የሥራ ፕሮግራሞች ላይ መክሮ ለሚኒስትሩ ያቀርባል ፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ነታቸውን ይከታተላል ፤

፮· ለዋናው ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ ሀላፊዎችን ሹመት ያጸድቃል ፤

፯· በየሦስት ወሩ ስለድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ ለሚኒስትሩ ሪፖርት ያቀርባል ።

፲· <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

፩· ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቦርዱ ሰብሳቢ ጥሪ ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል ቢያንስ አንድ ሦስተኛው ሲጠይቁ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

፪· በስብሰባው ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል ።

፫· ቦርዱ ውሳኔ የሚያስተላልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል። ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል ።

፬· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (፪) እና (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ቦርዱ የራሱን የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል።

፲፩· <u>የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· ዋና ሥራ አስኪያጁ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሥራ ይመራል ፤ ያስተዳድራል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ዋና ሥራ አስኪያጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ለድርጅቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል ፤

ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማዎች ተከትሎ ሚኒስትሩ በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሠራተኞች ይቀጥራል ፤ ያስተዳድራል ፤

ሐ) የድርጅቱን ዓመታዊ ረቂቅ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል ፤

8. *Members of the Board*

1) The Board shall have not more than members;
2) The Chairman and Members of the Board shall be designated by the government from pertinent institutions.

9. *Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the following powers and duties:

1) to follow-up and ensure the implementation of the objectives as well as the powers and duties of the agency provided in Articles 5 and 6 of this Proclamation;
2) to prepare and submit to the Minister the organizational structure and administrative directives of the Agency and ensure its implementation upon approval;
3) to review directives prepared by the Agency and ensure its implementation when approved by the Minister;
4) to devise ways on how to consolidate, expand and progress the activities of the Agency;
5) to review and submit to the Minister the plan, the draft budget and the work programme of the agency and follow-up regulate its implementation upon approval;
6) to approve the appointment of officials directly accountable to the General Manager of the Agency;
7) to report about the activities of the agency on every three months to the Minster.

10. *Meetings of the Board*

1) The Board shall have its regular meetings evey three months; extraordinary meetings may be convened any time when called by the Chairman or upon request of at least one third of the members.
2) There shall be a quorum where more than half of the members are present at the meeting of the Board.
3) Decisions of the Board shall be passed by a majority vote; in case of a tie, however, the Chairman shall have a casting vote.
4) Without prejudice to sub Articles (1), (2) and (3) of this Article, the Board may adopt its own rules of procedure.

11. *Powers and Duties of the General Manager*

1) The General Manager shall be the Chief executive officer of the Agency and shall, subject to the general directives given by the Board, direct and administer the activities of the Agency.
2) Without limiting the generality of the provisions of sub-Article(1) of this Article, the General Manager shall:
   (a) exercise the powers and duties vested in the Agency under Article 6 of this Proclamation;
   (b) employ and administer the employees of the Agency in accordance with directives to be issued by the Minster following the basic principles of the federal civil service law;
   (c) prepare and submit to the Board the annual draft budget and work programme of the Agency;

መ) ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጁ የሆኑ የድርጅቱን ሀላፊዎች በመምረጥ ለቦርዱ አቅርቦ ያጸድቃል፤

ሠ) ለድርጅቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል ፤

ረ) ድርጅቱን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል ፤

ሰ) በየሦስት ወሩ የድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል ።

፲፪· በጀት

የድርጅቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፤

፩· ድርጅቱ በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰበስበው የውሃና የአገልግሎት ክፍያዎች ፤ እና

፪· ከሌሎች ምንጮች ።

፲፫· የሂሣብ መዛግብት

፩· ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል ፤

፪· የድርጅቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ ።

፲፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከህዳር ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

(d) select and submit to the Board for approval officials of the agency accountable to the general Manager;

(e) effect expenditure in 'accordance with the approved budget and work programme of the agency;

(f) represent the agency in all its dealings with third parties;

(g) submit to the Board, quarterly report on the activities of the agency.

12. *Budget*

The budget of the agency shall be drawn from the following sources:

1) water charges and service fees collected in accordance with this Proclamation; and
2) any other sources.

13. *Books of Accounts*

1) The Agency shall keep complete and accurate books of accounts.
2) The books of accounts and financial documents of the Agency shall be audited by the Auditor General or by auditors designated by him.

14. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 10th day of November, 1998.

Done at Addis Ababa, this 10th day of November, 1998.

NEGASO GIDADA(DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE